# መልካም ጓደኛ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ አሜን

በዚህ በምንኖርበት አለም ይብዛም ይነስም አንድ ወይም ከዚያ በላይ ጓደኛ ይኖረናል። በእርግጥ በዚህ ጽሁፍ ዉስጥ ለመግለጽ የተፈለገዉ የወንድ ወይም የሴትን የተቃራኒ ፆታ የፍቅር ጓደኝነትን ሳይሆን መልካም የልብ ጓደኛ ማለት ምን ማለት ነዉ? የሚለዉን ለማየት ሲሆን ምናልባትም ብዙዎቻችን በተለምዶ እገሌ እኮ የእገሌ የልብ ጓደኛዉ ነዉ፤ እገሊትም ለእገሊት የልብ ጓደኛዋ ናት ስንልም እንሰማለን። በአንጻሩ ደግሞ አንዳንድ ሰዎች እገሌ ወይም እገሊት እኮ ጓደኛ አይወጣለትም ወይም አይወጣላትም እንዲያዉ ምክንያቱ ምን ይሆን? በማለት አስተያየት እንሰጣለን። ይሁን እንጅ የልብ ጓደኛ ብለን ስንናገር መለኪያችን ከምን አንጻር እንደሆነ መገንዘቡ የበለጠ የመልካም ጓደኛን ትርጉም እንድንረዳ ይረዳናል። ምክንያቱም ብዙ ሰዎች ጓደኛ የሚመርጡበትን መመዘኛ ካለማወቅ የተነሳ እንዲሁ ራሳቸዉ በቀመሩት የጓደኝነት መመዘኛ ቀመር አኳያ ብቻ ስለሚሆን በሆነ አጋጣሚ ካስቀመጡት ቀመር በተቃራኒ ኢምንት በሆነና እዚህ ግባ በማይባል ምክንያት በመካከላቸዉ የግጭት ፀሐይ ሲገባ የሚፈጠረዉ እሳትና ትርምስ አይድረስ ሲያስብል ይታያልና ነዉ። በቃ ነገሩ በሙሉ ይበላሻል፤ አብረዉ ያሳለፏቸዉ የደስታና የሀዘን ጊዜያቶች ከመቅጽበት በዜሮ ተባዝተዉ ባህር ዉስጥ እንደገባ ጨዉ ድራሻቸዉ ይጠፋና አይንህ ለአፈር አይንሽ ለአፈር ሲባባሉ ማየትና መስማት የተለመደ ነዉ። እንዲያዉም በጓደኛሞች መካከል የገባ ጸብ በቀላሉ አይበርድም፤ በቀላሉም አንዱ ለአንዱ ለይቅርታ እጁን አይዘረጋም። ምክንያቱም ሁለቱም ካላቸዉ ቀረቤታ አንጻር አንዱ የአንዱን፤ ሌላዋም የሌላይቱን ምስጢር ልቅምና ጥንቅቅ አድርገዉ ስለሚያዉቁት እሰራለታለሁ፤ እሰራላታለሁ፤ ደግሞ እርሱ፤ ደግሞ እርሷ ቆይ ቀን ያገናኘን ልኩን አሳየዋለሁ፤ ቆይ ልኳን አሳያታለሁ መባባል ሁሌም የሚታይ ገሀዳዊ ትዕይንት ነዉ።

እኛ ክርስቲያኖች ጓደኛ ስንመረጥ ከመንፈሳዊ ህይዎት አንጻር ምን መሆን አለበት? የሚለዉን ጥያቄ አስቀድመን ልንጠይቅ ይገባል። ምክንያቱም ስለ ጓደኛ ስናነሳ ጓደኛ በሰዎች ባህሪ ላይ ሊኖረዉ የሚችለዉን ጥሩም ይሁን መጥፎ፤ አሉታዊና አዎንታዊ ተጽኖዎችን መመልከቱ ከሁሉም በላይ አጽንኦት ልንሰጠዉ የሚገባን ጉዳይ ስለሆነ ነዉ። ከዚህ አንጻር ብዙ ጊዜ ሰዎች የአንድን ሰዉ ባህሪና ማንነት ለመረዳት ሲፈልጉ አብሮት የሚዉለዉን ሰዉ ወይም ዉሎዉ ከማን ጋር እንደሆነ ካወቁ በኋላ በቀላሉ ወደ ራሳቸዉ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ አይቸገሩም። ምክንያቱም አንድ አባባል አለ «ጓደኛህን ንገረኝና ማንነትህን እነግርሃለሁ»

የሚል። ስለሆነም አብረን የምንዉለዉ ጓደኞችን ዕለት ዕለት ለምናንጸባርቀዉ የባህርይ ለዉጥ የጎላ ድርሻ ይኖረዋል ማለት ነዉ። ስለዚህ ሁላችንም የተጠራነዉ በእግዚአብሔር ድንቅ አጠራሩ ለመንፈሳዊ ህይዎት፤ ጉዟችንም ወደ መንግስተ ሰማያት ለመድረስ እስከሆነ ድረስ መመሪያችንና አስተማሪያችን መጽሐፍ ቅዱስ ነዉና እርሱን ዋቢ አድርገን የጓደኛን ምንነትና ጥቅምና ጉዳቱን በእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል እየፈተሸን የጓደኝነት ህይዎታችን ምን እንደሚመስል እንመለከታለን።

ሁላችንም እንደምናዉቀዉ በጎ ጓደኛ እንዳለ ሁሉ ክፉ ጓደኛ ይኖራል። እነዲሁም ክፉ ጓደኛ እነዳለ ሁሉ በጎ ጓደኛም አለ። ከዚህ አንጻር ህይማኖተኛ ጓደኛ እነዳለ ሁሉ ከሀዲ ጓደኛም ይኖራል፤ ወደ ህይዎት የሚመራ ጓደኛ እንዳለ ሁሉ ወደ ሞት የሚመራ ጓደኛም አለ፤ ወደ ብርሃን የሚመራ ጓደኛ እነዳለ ሁሉ ወደ ጨለማ የሚመራ ጓደኛም አለ። ስለሆነም ጓደኛ ከመያዛችን በፊት ሁላችንም ጓደኞቻችን ስለሚሆኑ ሰዎች አስቀድመን ልንመረምር ይገባናል። ልበ አምላክ ዳዊት በመዝሙሩ እንደከተበዉ በመዝሙር 17፡25 ላይ «ከቸር ሰዉ ጋር ቸር ሆነህ ትገኛለህ፤ ከቅን ሰዉ ጋር ቅን ሆነህ ትገኛለህ፤ ከንፁሕ ሰዉ ጋር ንፁሕ ሆነህ ትገኛለህ፤ ከጠማማ ጋር ጠማማ ሆነህ ትገኘለህ» ይለናልና። በዚህም ቅዱስ ዳዊት ከምን አይነት ሰዉ ጋር ዉለን ምን አይነት ሰዉ ልንሆን እንደምንችል ይነግረናል። ምክንያቱም ሰዉ የሚመስለዉ ከጓደኛዉ ጋር ከሚኖረዉ መልካምም ይሁን መጥፎ በተላበሰዉ ባህሪ ነዉና።

እንግዲህ ልበ አምላክ ዳዊት በመዝሙሩ ከቸር ሰዉ ጋር ቸር ሆነህ ትገኛለህ ሲል፤ ንጽሐ ስጋን ከንጽሐ ነፍስ ጋር አንድ አድርጎ ከያዘ፤ በልቡናዉ ቅን ከሆነና የሰማዩን መንገድ እያሰበ፤ ዕለት ዕለት ምግባርና ትሩፋትን ገንዘቡ በማድረግ ከሀጢያትና ከበደል ከራቀ ሰዉ ጋር ከዋልላችሁ እነዚህን ሀብታት በሙሉ እናንተም በመተግበር በምግባር ትመስሉታላችሁ ሲለን ነዉ። በሌላ አነጋገርም ከቸር ሰዉ ጋር ቸር ሆነህ ትገኛለህ ሲል ንጽሐ ስጋን ገንዘባቸዉ አድርገዉ ምንም እንኳን በህሊናቸዉ የተለያየ ሀጢያት ቢመላለስም በትዕግስት ጸንተዉና ታግሰዉ ሁልጊዜም ረድኤተ እግዚአብሔርን እያሰቡ በህሊናቸዉ እየመጣ የሚያስጨንቃቸዉን ሀጢያት በገቢር ባለመፈጸም ሰይጣንን ድል ከሚያደርጉት ሰዎች ጋር ከዋላችሁ እናንተም ይህንን ጸጋ የማግኘት እድል ይኖራችኋል ማለቱ ነዉ። ከዚህ በተቃራኒዉ ደግሞ ሁልጊዜ ሀጢያትንና በደልን ከሚፈጽም ሰዉ ጋር ጓደኝነት መስርተን ብንኖር ነገ ከነገ ወዲያ እኛም ሀጢአትንና በደልን የምንፈጽም እንሆናለን ማለቱ ነዉ። ሌላዉ ደግሞ ከንጹሕ ሰዉ ጋር ንጹህ ሆነህ ትገኛለህ ማለቱ ነፍሱን ሳያቆሽሽ በንጽህና ጸንቶና ንጽህናዉን ጠብቆ ከሚኖር ጋር ጓደኝነትን ብትመሰርቱ የእርሱን አርአያ ምሳሌ ወስዳችሁ እንደሱ ንጽህናን ሀብታችሁ ታደርጋላችሁ፤ እናንተም ነፍሳችሁን በበደልና በክፋት ሳታረክሱ ብትኖሩ የዚያን ሰዉ ንጸህ ነፍስ አብነት አድርጋችሁ ከንጽህ ነፍስ ማዕረግ ትደርሳላችሁ ማለቱ ነዉ። እንደገናም ከቅን ሰዉ ጋር ቅን ሆነህ ትገኛለህ ሲል ንጽሐ ልቡና ካለዉና ልቡናዉን ቀድሶና

ከሀሳብ ሀጢያት ተለይቶ ክፉ ምኞት ከጠፋለት ሰዉ ጋር ጓደኝነትን ብትመሰርቱ ከእርሱ ምሳሌን በመዉሰድ ቀስ በቀስ በመንፈሳዊ ህይዎት በማደግ እንደሱና እንደሷ ንጽሐ ልቡናን ገንዘባችሁ ታደርጋላችሁ ማለቱ ነዉ። ንጽሐ ልቡና ላይ መድረስ እጅግ ታላቅ ብቃት ነዉ። ምክንያቱም ንጹህ ልቡና ያላቸዉ ሰዎች እግዚአብሔርን ማየት ይችላሉና ነዉ። ጌታችንና አምላካችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራ ላይ ስብከቱ ስለ አንቀጸ ብጹአን ሲያስተምር «ልበ ንጹሆች ብጹአን ናቸዉ እግዚአብሔርን ያዩታልና » ማቴ 5 ብሎናልና። ሌላዉና የመጨረሻዉ ከጠማማ ሰዉ ጋር ጠማማ ሆነህ ትገኛለህ ማለት ከከሀዲ ሰዉ ጋራ ጓደኝነት ከመሰረታችሁ ነገ ከነገ ወዲያ እናንተም ከሀዲ ትሆናላችሁ፤ ከተጠራጣሪ ሰዉ ጋር አብራችሁ ከዋላችሁ እናንተም በእኩይ ምግባሩ ተስባችሁ ተጠራጣሪና መናፍቅ ትሆናላችሁ፤ መንፈሳዊ ነገር ሲነገር ከሚቀልድና ቧልት ከሚያወራ ሰዉ ጋር ጓደኛ ከሆናችሁ እናንተም ነገ ከነገ ወዲያ በእግዚአብሔር ቃል የምትቀልዱ፤ በሀይማኖት የምትቀልዱ፤ በቤተክርስቲያን ስርዓት የምትቀልዱ፤ በቅዱስ ታቦቱና በቅዱስ ስዕላቱ የምትቀልዱና ቧልተኞች ትሆናላችሁ ሲለን ነዉ። እንግዲህ ከነብዩ እግዚአብሔር ከልበ አምላክ ዳዊት የምክር ቃል እንደምንረዳዉ የሰዉ ልጅ ከዕለት ዉሎዉ በመነሳት በመልካም ወይም በክፉ የጓደኛ ተጽእኖ ስር ሊወድቅ እንደሚችል ነዉ። ከዚህም በመነሳት ባጠቃላይ ከላይ ከዘረዘርናቸዉ የጓደኛ ተጽእኖዎች በመነሳት ጓደኝነትን በሁለት ከፍለን ይሄዉም መልካም ጓደኛ እና ክፉ ጓደኛ ብለን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አንድምታና ዋቢ አድርገን እንመልከታለን።

## መልካም ጓደኛ

## ስለ መልካም ጓደኛ ስናነሳ አስቀድመን የምንመለከተዉ

### 1ኛ/ የዳዊትንና የዮናታንን ጓደኝነት ይሆናል (1ኛ ሳሙ 20፡42)

ዮናታን ማለት ቅዱስ ዳዊትን ሊገድለዉ ያሳድደዉ የነበረ የእስራኤል የመጀመሪያዉ ንጉስ የሳኦል ልጅ ነዉ። ንጉስ ሳኦልን እግዚአብሔር ለእስራኤል ንጉስነት የቀባዉ ከምንም ነገር ከአህያ ጠባቂነት አንስቶ በእግዚአብሔር ወዳጅ በነብዩ ሳሙኤል አማካኝነት ነበር። 1ኛ ሳሙ 9 እና 10. ነገር ግን ንጉስ ሳኦል ከእግዚአብሔር ያገኘዉን የንግስና ክብርና ሞገስ፤ የእግዚአብሔርን ቃል ባለመጠበቅና ከምንም አንስቶ ከፍ ከፍ ያደረገዉን እግዚአብሔርን ከመከተል ፈቀቅ በማለት የስጋ ፍላጎቱንና የአይን አምሮቱን መከተል ጀመረ። እንደ ትእዛዙም ባለመሄድ የተሰጠዉን ጸጋ አቃለለ 1ኛ ሳሙ 13፡14 እና 1ኛ ሳሙ 15፡10-12። እኛም የስጋ ፍላጎታችንን እና የአይን አምሮታችንን ብቻ ከተከተልን የእግዚአብሔርን ጸጋ እንደምናጣ የሳኦል ታሪክ ያጠይቀናል። እንዲያዉም እግዚአብሔር አምላክ ሳኦልን ለእስራኤላዊያን በማንገሱ እስከመፀፀት እንደደረሰ በዚህ የመጽሐፍ ክፍል ዉስጥ እናያለን። በዚህም ምክንያት የእግዚአብሔርም ጸጋና ሀይል ንጉስ ሳኦልን ስለተለየዉ እርኩስ መንፈስ በላዩ ላይ ስልጥኖበት በየጊዜዉ ያስጨንቀዉ ነበር። ይህም ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር አምላክ ብላቴናዉን ዳዊትን ከበግ እረኝነት አንስቶ ለእስራኤል ንጉስ አድርጎ በመቀባት ስላነገሰዉ ንጉስ ሳኦል በቅናት ተነሳስቶ እግዚአብሔር አምላክ ቅዱስ መንፈሱን ያሳደረበትን ብላቴናዉን ንጉስ ዳዊትን ሊገድለዉ ያሳድደዉ ነበር። ከዚህ እንደምንረዳዉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያደረባቸዉን ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያምንና ቅዱሳንን የሚያሳድዱ ሁሉ እርኩስ መንፈስ ያደረባቸዉ ሰዎች እንደሆኑ እናያለን። ይሁን እንጅ የንጉስ ሳኦል ልጅ ዮናታን አባቱ ሊገድለዉ ከሚያሳድደዉ ከዳዊት ጋር የልብ ወዳጅና ጓደኛሞችም ስለነበሩ ይለናል። እንዲያዉም ዮናታን አባቱ ሳኦል ቅዱስ ዳዊትን ለመግደል የሚያወጣዉን እቅድ በሙሉ ቀድሞ እያወጣ እንደ ነፍስ ይወደዉ ለነበረዉ ለጓደኛዉ ለዳዊት በጎን መልዕክት እየላከና ምልክት እያሳየ የቅዱስ ዳዊትን ነፍስ ከሞት ይታደግለት ነበር።

መልካም ጓደኛ እንደ ዳዊትና እንደ ዮናታን ነዉ ስንል መቼም በምንኖርባት አለም ብዙዎቻችን ከማንናኛዉም ነገር በላይ ለስጋችንና ለዘራችን እናደላለን። ከዚህም የተነሳ ሰዎች በሚያገኙት አጋጣሚ ሁሉ ዘርን ስንቆጥሩ፤ የዝምድና ሀረግንና የጋብቻ ትስስራቸዉን እየመዘዙ ፍትህን ስያዛቡ፤ የተቸገሩትን ሲገፉ እንደሚገኙ ሀገር ያወቀዉና ፀሐይ የሞቀዉ ጉዳይ ነዉ። በተመሳሳይም ማናችንም ብንሆን እድሉን ብናገኝ ይህን ከማድረግ ወደኋላ አንልም። በሌላም መልኩ በጓደኝነትና በትዉዉቅ የምንሰራቸዉ ብዙ ጥፋቶችም አሉ። ይሁን

እንጅ በዚህ መልኩ እንደመከታ የገነባናቸዉ ዘመድ አዝማድና ጓደኞቻችን ማንነታችንን የሚፈታተንና ሰብዕናችንን የሚገዳደር ችግርና ፈተና ሲገጥመን በደህና ቀን ባስቀመጥናቸዉ የከፍታ ማማ ላይ ሳይገኙ ወዲያዉኑ ሽርተት በማለት ፊታቸዉን ሲያዞሩብንና በራቸዉን ጥርቅም አድርገዉ ሲዘጉብን ስንመከት ደግሞ ችግራችንና ሀዘናችንን የበለጠ የከፋ ያደርገዋል። ዮናታን ግን ንጉስ ዳዊትን በችግሩ ጊዜ አልካደዉም፤ በችግሩ ጊዜ አልተንሸራተተበትም፤ በችግሩ ጊዜም አልተለወጠበትም። እንዲያዉም ምንድን ነበር ያለዉ? ወዳጄ ዳዊት ሆይ አባቴ እንደሚያሳድድህ አዉቃለሁ፤ በአባቴም እጅ ብትወድቅ እደሚገድልህ አዉቃለሁ፤ አለና እኔ ግን «አልክድህም አልለወጥብህምም» በማለት ቃል ኪዳኑን የበለጠ አፀናለት። እንዲያዉም አስቀድሞ አባቱ ንጉስ ሳኦል የሚያወጣዉን እቅድ ለንጉስ ዳዊት እየላከ ጓደኛዉ ዳዊት ከሞት የሚያመልጥበትን መንገድ ያመቻች ነበር። መልካም ጓደኛ ማለት ከጥፋት የምንርቅበትንና ከሞት የምናመልጥበትን መንገድ እንደ ዮናታን የሚያመቻችልንና የሚመክረን መሆን አለበት። ቂም በቀልህን ተዉ፤ ወደ ቤተ እግዚአብሔር ሂድ፤ ቅዱስ ቃሉን ስማ፤ ንስሀ ግባ ቅዱስ ስጋዉን ክቡር ደሙን ተቀበል እያለ እንደ ዮናታን ከሞት እንድናመልጥ የሚመክረን ጓደኛ መሆን አለበት። ምክንያቱም በሀጢያት መኖር ሞት ነዉ፤ የሀጢያት ደሞዝ ደግሞ ሞት ነዉ። ለዚያዉም የዘላለም ሞት። ስለሆነም የምንይዘዉ ጓደኛ እንደ ዮናታን ከሞት ወደ ህይዎት የሚመልሰን መሆን አለበት።

## 2ኛ/ የፊልጶስና የናትናኤል ጓደኝነት (ዮሐ. 1፤46)

በዚህ ክፍል ዉስጥ የፊልጶስንና የናትናኤልን ጓደኝነት እንመለከታለን። ፊልጶስ ከቤተ ሳይዳ መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የተከተለ ደቀ መዝሙርና ሀዋርያ ነዉ ዮሐ 1፡46። እርሱም ሁሉን እርግፍ አድርጎ ትቶ የህይዎት ባለቤት የሆነዉን መድህን አለም ክርስቶስን የተከተለ ነዉ። ምክንያቱም የሰማይና የምድር ፈጣሪ የሆነዉን ኢየሱስ ክርስቶስን ለመከተል ሁሉንም የስጋ አምሮቱን፤ የአይን ፍላጎትን፤ ከፋትን፤ ምቀኝነትን፤ ለሰዎች የሞት ጉድጓድ መቆፈርንና ባጠቃላይ የስጋ ፍሬያትን እርግፍ አድርጎ መተዉ ያስፈልጋልና። ይሁን እንጅ ቅዱስ ፊልጶስ እኔ ብቻ ክርስቶስን አግኝቼዋለሁ፤ እኔ ብቻ የዘላለም ህይዎት ላግኝ፤ እኔ ብቻ የህይዎት ራስ የሆነዉን ክርስቶስን ልከተል አላለም። ይልቁንም ዘወር ብሎ የልብ ጓደኛዉንና ባለንጀራዉን ናትናኤልን ጠራዉ፡- «ሙሴ በህግ ነቢያትም ስለ እርሱ የጻፉለትን የናዝሬቱን ኢየሱስን አግኝተነዋል በማለት» ዮሐ 1፡47። ናዝሬት የአመጸኞች መንደር ናት፤ ናዝሬት የከፉዎችና የወንበዴዎች መንደር ናት፤ ናዝሬት የአመንዝራዎችና የሴተኛ አዳሪዎች መንደር ናት። ከዚህ አንጻር ናትናኤል በጓደኛዉ በፊልጶስ ንግግር ተገርሞ እንዴትስ ናዝሬትን ከመሰለ በበጎ ሳይሆን በክፉ ተግባሯ ከምትታዎቅና በመጥፎ ስም ከምትጠራ ከተማ ክርስቶስን የሚያክል ንጽህ ባህርይ ጌታ ሊገኝባት ይችላል? ብሎ ጥቂት አሰበና ናዝሬትን መመርመር ጀመረ።

ከዚያም አንተ ፊልጶስ በዉኑ ከናዝሬት መልካም ነገር ሊወጣ ይችላልን? ሲልም ጠየቀዉ። ይህ የናትናኤል ጥያቄ ዛሬ ሁላችንም የምንጠይቀዉ ጥያቄ ነዉ። ብዙዎቻችን ባዙ ጊዜ ክፉ ስራ ከሚሰራበትና አልባሌ ከሚባል ቦታ በጎ ነገር የሚገኝ አይመስለንም። አልባሌ ከሚመስለን የሀጢያት ሰፈር እየኖረ ነፍስና ስጋዉን እያስጨነቀ ግን ለእግዚአብሔርና ለቅዱስ ቃሉ ክብር በመስጠት ሰማያዊ ዋጋ የሚያገኝ ብዙ ሰዉ አለ። ጻድቁ ሎጥ በሰዶምና ገሞራ ሲኖር የሀገሩ ህዝቦች ለአእምሮ የሚዘገንን የዝሙት ሀጢያትን ሲፈጽሙ በክፉ ስራቸዉ እንዳይተባበር ነፍሱን እያስጨነቀ አንድ እሱ ብቻ የእግዚአብሔር ሰዉ ሆኖ እንደኖረ ለአብነት ማንሳት ይቻላል ዘፍጥ 19። ግርግርና ወከባ ካለበት አካባቢ ጻድቅና በጎ ህሊና ያለዉ ሰዉ የሚገኝ አይመስለንም። ለዚህ ነበር ናትናኤልም በየዋህነት በዉኑ ከናዝሬት መልካም ነገር ሊወጣ ይችላልን? ሲል ፊልጶስን የጠየቀዉ። ይሁን እንጅ ፊልጶስ ናትናኤልን ለማሳመን ምንም አልተከራከረዉም ነበር። ብቻ መጥተህ እይ በማለት እጁን ይዞ ወደ አለም ቤዛ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ወሰደዉ እንጅ። በዚህ ጊዜ ነበር መድሃኒታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ናትናኤልን ሲያየዉ ስለ ናትናኤልም ፊልጶስ እስኪነግረዉ ሳይጠብቅ፦ «ተንኮል የሌለበት በእዉነት የእስራኤል ሰዉ እነሆ» አለ። ምክንያቱም እርሱ ልብ ያመላለሰዉን ኩላሊት ያጤሰዉን መርምሮ የሚያዉቅ ስለሆነ። ስንኳንስ የናትናኤል ስም የራሳችን ፀጉር እንኳን በእርሱ ዘንድ የተቆጠረ ነዉና። ተንኮል የሌለበት ሲል በልቦናዉ ቂም በቀል፤ በልቡናዉ ክፋት፤ በልቡናዉ ተንኮል የሌለበት የዋህ እስራኤላዊ ማለቱ ነበር። ናትናኤል ግን ይህን ሲሰማ ግራ ተጋብቶ የት ታዉቀኛለህ? ሲል መለሰለት። መድህን አለም ክርስቶስ ግን ገና ፊልጶስ ሳይጠራዉ ከበለስ በታች እያለ እንደሚያዉቀዉ አንድም ጌታችንና መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አለምን ለማዳን በግብረ መንፈስ ቅዱስ ያለ ዘርዐ ብዕሲ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በድንግልና ተፀንሶ በድንግልና በቤተልሄም በከብቶች ግርግም በተወለደ ጊዜ ሄሮድስ በቅናት ተነሳስቶ አስራ አራት እልፍ የቤተልሄም ህፃናትን ደም እንደ ጎርፍ ሲያፈስ የናትናኤል እናት ልጇን እንዳይገድሉባት በኮባ ቅጠል ጠቅልላ ከበለስ ስር ደብቃዉ ነበርና ከሄሮድስ እልቂት ያተረፍኩህ እኔ ነኝ ስላለዉ በዚች ግልጽና አጭር ምስጢር ናትናኤል ጌታዉን ወዲያዉኑ አመነዉ። ክርስቶስም መልሶ በናትናኤል እምነት ተገርሞ፦ በዚች በትንሺ ነገር አመንክን? ገና ከዚህ የሚበልጥ ነገር ታያለህ ሰማይ ሲከፈት፤ ቅዱሳን መላእክት በሰዉ ልጅ ላይ ሲወጡና ሲወርዱ ታያለህ ተከተለኝ አለዉ። በጥቂቱ ታመን በብዙ እሾምሀለሁ ያለ አምላክ እሱ ነዉና ማቴ 25፡21። ናትናኤልም እስከመጨረሻ ተከተለዉ ዮሐ 1፡52። ከዚህ ትምህርት የምንማረዉ ትልቅ ቁም ነገር አለ። ይሄዉም ፊልጶስ ናትናኤልን እጁን ይዞ ወደ እግዚአብሔር አመጠዉ ከመድሃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋርም አስተዋወቀዉ እርሱ አግዚአብሔር ነዉና። ዛሬ የብዙዎቻችንን መንፈሳዊ ህይዎት ስንመለከት እጅግ ያሳዝናል። ሹልክ ብለን ለብቻችን ወደ ቤተ እግዚአብሔር እንመጣለን እንጅ ሌሎች ጓደኞቻችንን ይዘን ስንመጣ አንታይም፤

በሌላም አንጻር ብንመለከት አንዳንዶች ጓደኞቻቸዉን ይዘዉ ወደ ጭፈራና መጠጥ ቤት ሲሄዱ ይታያሉ፤ ሌሎቹም ጓደኞቻቸዉን ይዘዉ ወደ አልባሌ ቧልትና ወሬ እንዲሁም ዋዛ ፈዛዛ ወዳለበት ለስጋም ሆነ ለህሊና ወደማይመች ቦታ ይሄዳሉ። በአንጻሩ ግን እንደ ፊልጶስ ያለ ጓደኛ ቢኖር ግን ጓደኛዉን ና እስኪ ዛሬ ቅዳሴ አለ፤ ና ዛሬ የሰርክ ጉባኤ አለ፤ ና የፅድቅ ስራን አንስራ እንጹምና እንጸልይ፤ እንመጽዉትና ንስሀ አንግባ፤ ና የክርስቶስን ስጋና ደም እንቀበል በማለት ከሀጢያት ህይዎት ወደ ጽድቅ ህይዎት በማምጣት ጓደኛዉ የዘላለም ህይዎት እንዲያገኝ ያደርጋል ዮሐ 6፡53-59። መልካም ጓደኛ በዚህ ይለካልና።

## 3ኛ/የሉቃስና የቀለዮጳ ጓደኝነት ሉቃ 24፡13

ሉቃስና ቀለዮጳ የልብ ጓደኛሞች ነበሩ። እነዚህ ጓደኛሞች ኗሪነታቸዉ ኤማሁስ ተብላ በምትጠራ ከኢሩሳሌም አቅራቢያ በስተ ሰሜን 12 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ባለች ከተማ ነበር። ጌታችንና መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለኛ ሲል በፈቃዱ መከራ ሞትን በተቀበለ በሶስተኛዉ ቀን ከኢየሩሳሌም ከተማ ተነስተዉ መኖሪያቸዉ ወደ ነበረችዉ ወደ ኤማሁስ ከተማ ጉዟቸዉን ባደረጉበት ወቅት እየደከሙና ጉልበታቸዉ እየዛለ፤ በድካም አካላቸዉ እየደከመ ሲሄዱ ወሬያቸዉ ሁሉ ስለ መድህን አለም ክርስቶስ መከራና ሞት ብቻ ነበር። አይሁድ አንዴት በሀሰት እንደከሰሱት፤ አንዴት መከራ እንዳጸኑበት፤ ስጋዉ አልቆ አጥንቱ እስኪቆጠር ስድስት ሽህ ስድስት መቶ ስድሳ ስድሰት ጊዜ ግርፋት እንደገረፉት፤ እንዴት መስቀል አሸከመዉ ከልጦስጥራ እያዳፉና እያሰቃዩ እስከ ቀራኒዮ እንደወሰዱት፤ እንዴት አይሁድ እንደዘበቱበትና ጸያፍ ምራቃቸዉን እንደተፉበት፤ ያም አልበቃ ብሏቸዉ በአምስት ችንካር በመስቀል ላይ ቸንክረዉ እርቃኑን እንደሰቀሉት እያሰታወሱ ልባቸዉ በሀዘን እየደማ ይጓዙ ነበር። እዉነቱን እንነጋገር ከተባለ እኛን በነዚህ በሁለቱ ጓደኛሞች ሉቃስና ቀለዮጳ ቦታ ላይ አስቀምጠን እንመርምር ብንል ስንኳንስ እንደነ እርሱ በድካም ስሜት ዉስጥ ሆነን ይቅርና በተመቻቸ ጊዜ አንኳን በተለያዩ አጋጣሚዎች ከጓደኞቻችን ጋር ስንገናኝ ማዉራት የሚቀናን ስለ ግል ህይዎታችን፤ ማለትም ስለ ትምህርት ደረጃችንና ስንት ዲግሪ እንዳለን፤ ስለምናገኘዉ ደሞዝና ስለትዳራችን፤ ስለስራ ወይም ስለ ግል ዝናችን እንጅ እግዚአብሔር ስላደረገልን ዉለታዉ፤ ስለማይነገር ስጦታዉ ወይም ስለከፈለልን ቤዛነትና ሀጢአታችንን ታግሶ እስከ መስቀል ሞት እኛን የወደደበትን ታላቅ ፍቅሩን ለአንድ ሴኮንድ እንኳን ለመናገር ፍላጎት የለንም። እነዚህ የኤማሁስ መንገደኞኛች ሉቃስና ቀለዮጳ ግን አንጀታቸዉ እየተንሰፈሰፈና ልባቸዉ በሀዘን እየደማ ከፉዎች አይሁድ እንዴት ያንን ሁሉ ግፍ ሲያደርሱበት፤ አንዲትም ቃል ሳይተነፍስ ፊቱና አካሉ በደም አበላ ተነክሮ ሊታረድ እንደሚወሰድ በግ እየወደቀ እየተነሳ፤ የሾህ አክሊል በራሱ ላይ ተደፍቶበት የተቀበለዉን መከራ እያሰቡ ከልባቸዉ በሀዘን መቃጥል የተነሳ ፊታቸዉ እስኪጠወልግ ድረስ ሞቱን

እያሰቡ ሲነጋገሩ ነበር። በዚህ ጊዜ ግን አንድ ሰዉ ወደ እነሱ ጠጋ ብሎ እንናንተ? አንደዚህ ፊታችሁ እስኪጠወልግና በሀዘን እሰክትዝሉ ድረስ ስለምን ታወራላችሁ? ሲል ጠየቃቸዉ። እነሱም ጥያቄዉን በጥያቄ መልሰዉ አንተ ደግሞ ለኢየሩሳሌም አዲስ ነህን? እኛማ የምናወራዉ በእግዚአብሔርና በህዝቡ ፊት በስራና በቃል ብርቱ ስለነበረዉ ስለናዝሬቱ ኢሱስ ክርስቶስ ነዉ። እርሱንም የእስራኤል አለቆችና መኳንንቶቻችን ለሞት ፍርድ አንዴት እንደሰጡትና እንደሰቀሉት ነዉ። እኛ ግን እስራኤልን እንዲቤዥ ተስፋ አድርገን ነበር። ይህ ሁሉ ከሆነ ዛሬ ሶስተኛዉ ቀን ነዉ። ይሁን እንጅ አንዳንድ ከእኛ ጋር አብረዉ የነበሩ ሴቶች ማልደዉ ሄደዉ ስጋዉንም ባጡ ጊዜ ሕያዉ ነዉ የሚሉ የመላዕክትን ራዕይ አየን ሲሉ መጥተዉ ነበር። እያሉ ያዩትንና የሰሙትን ሁሉ በነገሩት ጊዜ ጌታ ምን አላቸዉ፡- እናንተ ነብያት የተናገሩትን ከማመን ልባችሁ የዘገየ በማለት የነቢያትን ትንቢት እያነበበ፤ ያነበበዉንም እየተረጎመ፤ የተረጎመዉንም እያመሳጠረ ሲነግራቸዉ አፈ ልቦናቸዉን ከፍተዉ የሰሙት ነበር። በዚህ ጊዜ ነበር እሱ ሲያስተምራቸዉ፤ እነሱም ልባቸዉን ከፍተዉ፤ አእምሮአቸዉን አንቅተዉ ሲማሩ ፀሐይ ባቆለቆለች ጊዜ አልፏቸዉ ሌላ ሩቅ ሀገር የሚሄድ ስለመሰላቸዉ ቤት የእግዚአብሔር ነዉ። አንተም የእግዚአብሔር እንግዳ ነህ ግባና ከእኛ ጋር እደር ብለዉ ግድ አሉት ይለናል ሉቃ.24፡29 ። መድህን አለም ክርስቶስም በቤታቸዉ በእንግድነት ገባ። ከዚያም እንደ እብራዊያን ልማድ ማዕድ አቅርበዉ በእንግድነት የመጣ እንግዳ ጸሎት አድርሶ፤ ቡራኬ ቆርሶ፤ ማጉረስ ባህልና ወግ ነዉና ባርከህ ቀድሰህ ስጠን አሉት። ጌታም እንጀራዉን ባርኮና ቀድሶ ቆርሶ ሲሰጣቸዉ አይነ ልቡናቸዉ ተከፈተ። በዚህ ጊዜ አይነ ልቡናቸዉ ሲከፈት በእንግድነት እቤታቸዉ ገብቶ አብሯቸዉ ያለዉ መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን አወቁት። ከዚያም ወዲያዉኑ ተሰወረባቸዉ። ያን ጊዜ እንዴት ያናድዳል? በማለት ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ የሚሰጣቸዉን ተስፋ አስታዉሰዉ ከተስፋዉ ዉጭ እንዳይሆኑ በማሰብ እየደከሙ የተጓዙትን ያንን ሁሉ መንገድ ለድካማቸዉ የክርስቶስ ተስፋ ብርታት እየሆናቸዉ እንደገና ወደ ኢሩሳሌም ተመለሱ። ሉቃ 24፡13-35። መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሀዋርያቱ የሚሰጣቸዉ ተስፋ ምን የሚል ነበር? ቢሉ «እነሆም አባቴ የሰጠዉን ተስፋ እኔ እልክላችኋለሁ፤ እናንተ ግን ከላይ ሀይል እስክትለብሱ ድረስ በኢሩሳሌም ከተማ ቆዩ» ሉቃ 24፡49 የሚል ነበር። ታዲያ ሉቃስና ቀለዮጳም ከዚህ ከተስፋዉ ቃልም ተካፋዮች ሆኑ፤ በፍጻሜዉም ቅዱስ ሉቃስ የሉቃስ ወንጌልን፣ ግብረ ሐዋርያትን የሚያክል የሀዋርያትን ገድል ቅዱስ መጽሐፍ ለመጻፍ ቻለ። እኛስ ከዚህ ምን እንማራለን? ሉቃስና ቀለዮጳን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እያወሩ በነበረበት ሰዓት ኢየሱስ ክርስቶስ በመካከላቸዉ ተገኝቶ አነጋገራቸዉ፤ አስተማራቸዉ፤ ሚስጠራቱን ተረጎመላቸዉ፤ በቤታቸዉም እንግዳ ሆኖ ገባ፤ ምግባቸዉንም ባረከላቸዉ፤ የተባረከዉንም ምግብ ከአምላካቸዉ ከክረስቶስ እጅ ተቀበሉ፤ አይነ ልቡናቸዉም ተከፈተላቸዉ። እኛም በቤታችንም ሆነ በማንኛዉም በምንገናኝበት ቦታ ስመ እግዚአብሔርን ርዕሳችን አድርገን ልዩ

የሆነዉን መግቦቱን፤ እየሞተ ህይዎት የሰጠንን፤ ቃላቶች የማይገልጹትን እስከ መስቀል ሞት የከፈለልንን የቤዛነት ፍቅሩንና ይቅር ባይነቱን፤ ሀጢያተኞች ሳለን እንደ በደላችን ፈጥኖ ያላጠፋበትን ተዕግስቱን፤ እያነሳን እርስ በርሳችን ብንነጋገር ለሌላዉም ብናወራ እግዚአብሔር ሁሌም ከእኛ ጋር ይሆናል። መልካም ጓደኛ ማለት በማንኛዉም ጊዜ ሲገናኝ የሆነ ያልሆነ አለማዊ የወሬ ርዕስ መርጦ መነታረክና ዱላ ቀረሽ ጨቅጭቅ በመፍጠር በመጨረሻም አላስፈላጊ አምባጓሮ ዉስጥ የሚገባና የሌላዉን ሰዉ ስም በከንቱ እያነሳ በሀሜት ቢላዋ ስጋቸዉን የሚቦጨቅ፤ በሀሜት ጽዋ ደሙን የሚጠጣ ሳይሆን ጥሩና መልካም ጓደኛ ሲገናኝ ሁሌም ስመ እግዚአብሔርን በመጥራት የቅድስናን ስራ ለመስራት የሚያስችሉ ሀሳቦችን በማንሳት ሉቃስንና ቀለዮጳን አርአያዉ የሚያደርግ መሆን አለበት።

## ክፍል ሁለት

## ጠማማ እና ክፉ ጓደኝነት

ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ከንጹህ ሰዉ ጋር ንጹህ ሆነህ ትገናለህ፤ ከቸር ሰዉ ጋር ቸር ሆነህ ትገኛለህ ካለ በኋላ ከክፉ ሰዉ ጋር ክፉና ጠማማ ሰዉ ሆነህ ትገኛለህ ብሏልና የክፉና የጠማማን ጓደኛ መጨረሻ ዉጤቱ ምን እንደሚመስል ደግሞ እንመልከት፡-

የሁላችንም የመንፈሳዊ ህይዎታችን መመሪያ በሆነዉ የመጽሀፍ ቅዱስ ትምህርት ዉስጥ ከላይ በጠቀስነዉ መልኩ እዉነተኛ የልብ ጓደኞች በብዙ የመጽሐፍ ክፍል ዉስጥ እንደተጠቀሱ ሁሉ እኩይ ክፉና ጠማማ ምክራቸዉ ያጣመማቸዉ፤ ጠማማ ጓደኛ ያቆሰላቸዉ፤ በጠማማ ምክር ተመርተዉ እግዚአብሔር የማይወደዉን ድርጊት በመፈጸም ከእግዚአብሔር ልጅነት በመለየት በስጋም ሆነ በነፍስ እንዲፈረድባቸዉ የተደረጉ የጠማማ እና የክፉ ጓደኛ ሰለባ የሆኑ አያሌ ሰዎችንም እናገኛለን።

### ፲ኛ/ የሔዋንና የእባብ ጓደኝነት (ዘፍ 3፡48)

በዚህ የመጽሐፍ ክፍል ዉስጥ የሄዋን ጓደኛ አዳም፤ የአዳምም ጓደኛ ሔዋን እንደሆነች እናያለን። ምክንያቱም አዳምን ለሔዋን፤ ሔዋንንም ለአዳም ያዘጋጀ እግዚአብሔር አምላክ ነዉና። ይሁን እንጅ አዳምና ሔዋን እግዚአብሔር አምላክ ካዘጋጀላቸዉ ጓደኝነት ወጥተዉ በጎን የእባብን ጓደኝነት ያዙ። እባብ ደግሞ በስነ-ፍጥረት ትምህርት እንደምረዳዉ ተንኮለኛ ነበረች ይለናል። ዘፍ 3፡1። ምንግዜም ቢሆን በተንኮለኛና በጠማማ ልብ ዉስጥ ሙሉ ስልጣን ያለዉ ሰይጣን ነዉና አዳምና ሔዋንን እግዚአብሔርን ከሚያክል ሀያል ጌታ፤ ገነትን ከመሰለች ልዩ ቦታ ሊለያቸዉ ሲፈልግ በተንኮለኛ በእባብ ልብ አድሮ በግልጽ ሰይጣንነቱን ሳይገልጽ ወደ ቄያቸዉና እግዚአብሔር አምላካቸዉን ወደሚያነጋግሩባት፤ ሁሉንም እንስሳትና እፅዋትን ወደሚያስተዳድሩባት ወደ ገነት ርስታቸዉ ሰተት ብሎ ገባ። ገብቶም አልቀረም የልቡን መሻት ለመፈጸም ስራዉን ጀመረ። መቼም በዚች ባለንባት አለም ሁላችንም እንደምናዉቀዉ ጠማማና ክፉ ልቦና ያለዉ ሰዉ በድብቅ የያዘዉን ክፉ ሃሳብ ለመፈጸም ሲፈልግ አንደበቱን አሳምሮ ለሰዎች የሌላቸዉን ክብር እየጨማመረ፤ ልባቸዉን በከንቱ ዉዳሴ ካስሸፈተ በኋላ ጠልፎ በመጣል ወደ ገደል ይጨምራቸዋል። ሰይጣን የተባለዉ ዲያብሎስም ለአዳምና ለሔዋን ያቀረበላቸዉ ሰላምታ «አ አዳም ንጉሰ ሰማይ ወምድር፤ አዳም የሰማይና የምድር ጌታ» እንደገናም ሄዋንን «አ ሔዋን ንግስተ ሰማይ ወምድር፤ ሔዋን የሰማይና የምድር ንግስት» ነሽ የሚል ነበር። ይሁን እንጅ አዳምና ሔዋን ይህንን የሰይጣን ከንቱ ዉዳሴ ሲሰሙ በመቃወም ፋንታ ተቀበሉት በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር አምላክ

እንዳያደርጉት የሰራላቸዉን ትእዛዝ በመተላለፍ ሞትን በራሳቸዉና በልጅ ልጆቻቸዉ እንዳመጡ። እኛም በመንፈሳዊ ህይዎት እንመላለሳለን ከምንል ሰዎች ሳይቀር የልብ ወዳጅ ለማድረግ የምንመርጠዉ ሰዉ ደካማ ስራችንን እያነሳ የሚገስጻንን ሳይሆን የሌለንን ክብር በላያችን ላይ እየከመረ የሚያሞግሰንና በከንቱ ዉዳሴ የሚጠልፈንን ሰዉ ነዉ። እባብ አዳምንና ሔዋንን ከማዕረጋቸዉ እንዲወርዱ፤ ከክብራቸዉ አንዲሻሩ፤ ከገነት አንዲባረሩ ያደረጋቸዉ የሌላቸዉን ክብር እጅግ በሚያምር አነጋገር በመናገር ነበር። ዛሬም አለማችንን የሞሏት ብዙ አይነት እባቦች ናቸዉ። ልስልስ ባለና በሚያቀላምጥ ንግግር ሰዎችን ከእናት ቤተክርስቲያናቸዉ የኑፋቄ መርዝ በመርጨት አስኮብልለዉ የሚያስወጡ፤ የትዕቢት መርዝን የተሞሉ፤ የቅናት መርዝን የተሞሉ፤ የሀሜት መርዝን የተሞሉ፤ የጥርጠርና የክህደት መርዝን የተሞሉ ግን እኛ ጓደኛ አድርገን የያዝናቸዉ አያሌ ሰዎች አሉ። ከዚህ አንጻር እኛም እነዚህ ሰዎች እንዳይመርዙንና ከህይዎት መንገድ ወደ ኋላ እንዳያስቀሩን፤ በነርሱ መጥፎ ምግባር ተስበን ከእግዚአብሔር ክብር እንዳንርቅ፤ በእነሱ ክፉ ስራ ተስበን በገነት ከተመሰለች ከቅድስት ቤተክርስቲያን እንዳንወጣ፤ በክፉ ምክራቸዉ ተስበን በቤተመቅደስ የተመሰለ ሰዉነታችንን ስናቆሸሸ ስንረክስ እንዳንገኝ ልንጠነቀቅ ይገባል። የአባታችን የአዳምና የእናታችን የሄዋን ታሪክ ከታሪክነቱ ባሻገር የሚያስተምረን ከዉድቀታቸዉ በመማር የህይዎት አቅጣጫችንን እንድናስተካክል ነዉና።

## 2ኛ/ የዲና እና የአሕዛብ ልጆች ጓደኝነት (ኦሪ ዘፍጥ 34፡1-31)

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ዉስጥ የጻድቁና የእምነት አባት የሆነዉን የአብርሐምን የልጅ ልጅ የቅዱስ ያዕቆብን አንድና ብቸኛ ሴት ልጁን የዲናን የጎደፈ ታሪክ እንመለከታለን። ዲና ማለት ብኩርናን ከታላቅ ወንድሙ በመጀመሪያ በምስር ወጥ፤ በኋላም በእናቱ በርብቃ ምክር አማካኝነት በረከትንና ምርቃትን ከኤሳዉ የወሰደ፤ መጨረሻም በህልሙ ከእግዚአብሔር ጋር ሲታገል ያደረና እግዚአብሔርን «ካልባረከኝ አለቅህም» በማለቱ እግዚአብሔር አምላክ ታግለህ አሸንፈኸኛልና ስምህ ያዕቆብ ሳይሆን እስራኤል ተብሎ ይጠራል ያለዉ የጻድቁ የያዕቆብ ብቸኛ ሴት ልጁ ናት። ይሁን እንጅ ከዚህ የጻድቅ ቤተሰብ የተወለደችዉ ዲና እየቆየች ስትሄድ ከአህዛብ ልጆች ጋር ጓደኝነትን መሰረተች። ብርሃናተ አለም ቅዱስ ጳዉሎስ «አትሳቱ ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋል» 1ኛ ቆሮ 15፡33። እንደሚለን ከመልካም ቤተሰብ ይዛዉ ያደገችዉን የእግዚአብሔር ልጅነት በአምልኮትም ሆነ በሃይማኖት ከማይመስሏት አምልኮታቸዉ ጣዖት፤ ጌጣቸዉ ዝሙት ከሆኑት የአህዛብ ልጆች ጋር ጓደኝነትን መስርታ ከእነርሱ ጋር ወጣ ገባ ማለት ጀመረች። ብዙም ሳትቆይ ከአህዛብ ሴቶች ልጆች ጋር የመዋሏ ነገር ሌላ መዘዝ ይዞባት ከተፍ አለና ከዕለታት በአንዱ ቀን አንድ የአህዛብ ጎረምሳ ድንግልናዋን ወስዶ አስነወራት፤ ከክብርም አሳነሳት። ዲና ጥሩ ጓደኛ ባለመምረጧ

ለቤተሰቦቿና ለዘመዶቿ ማፈሪያ እስከመሆን ደረሰች። በሌላም መልኩ ዝሙት በእግዚአብሔር ዘንድ አስቀያሚና አስጸያፊ ስለሆነ ረክሳና ቆሽሻ ተገኘች። ዛሬም ብዙ እህቶቻችንና ወንድሞቻችን በቤተክርስቲያን ጥሩ መንፈሳዊ ህይዎትን ጀምረዉና ለመዳኑ ህይዎት በክርስቶስ ፍቅር ተጠርተዉ የሰማያዊ ክብር ተካፋይ ከሆኑ በኋላ ከመጥፎ ጓደኛ ጋር ገጥመዉ ለማይገባ ግብር የተዳረጉ፤ ከእግዚአብሔር ክብር ተለይተዉ ለአዕምሮ የማይገባን ግብር እንኳን በመፈጸም ለሞት ፍርድ የሚገባ የሀጢያት ስራን በመስራት ከጸጋዉ የተራቆቱ ሰዎች አያሌ ናቸዉ። ስለሆነም ከዲና ታሪክ ምን እንማራለን? ተምረንስ ከእንደዚህ አይነቱ በሀጢያት ከሚመጣ ሞት ራሳችንን ልንጠብቅና ሁሌም ቢሆን በእግዚአብሔር ልንታመንና ከጸጋዉ እንዳንለይ ጓደኞችን ስንመርጥ ምን ያህል እንጠነቀቃለን?። መልሱ ቀላል ነዉ በሀጢያት ወድቀን ሰዉንም እግዚአብሔርንም እንዳናሳዝን ከዲና አሳዛኝ ታሪክ ተመረን አብረናቸዉ የምንዉላቸዉን ጓደኞች በጥንቃቄ ልንመረምር ይገባል። ብልህ ልጅ በሰዉ ስህተት ይማራል ሰነፍ ልጅ ግን ከራሱ ስህተት አይማርም እንዲሉ የሚነገረዉ ቅዱስ ቃል ለህይዎት ነዉና በእምነት ከማይመስሉን፤ በምግባር ከማይመጥኑን ሰዎች ጋር አላስፈላጊ ጓደኝነት እንጠበቅ።

## 3ኛ/ የቅዱስ ዳዊት ልጅ የአምኖንና የኢዮናዳብ ጓደኝነት (2ኛ ሳሙኤል 13፡1-19)

አምኖን የቅዱስ ዳዊት ልጅ ነዉ። ይሁን እንጅ ሰዉ ሆኖ የማይፈተን የለምና በአባቱ በኩል ከምትወለደዉ በገዛ እህቱ በትዕማር ፍቅር ተፈተነ። ከገዛ እህቱ ከትዕማር ጋራ ፍቅር ስለያዘዉ ምግብ አልበላህ፤ ዉሀ አልጠጣህ አለዉ። ከሳ መነመነ የሚይዘዉን የሚጨብጠዉን አጣ፤ ሲተኛም ሲነሳም ሁሌም የሚያስበዉ እሷን በቻ ሆነ። ያዳቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይተዉም እንዲሉ አባቶቻችን የክፉ ሰሪ ሰይጣንን መጠን የሌለዉ መሰሪነት በሚገልጹበት ብሂላቸዉ ክፉ ስሜቱን ብቻ መከተል ጀመረ። በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ዉስጥ እያለ ጭንቀቱን የሚጋራለት የሚመክረዉ ጓደኛዉን ኢዮናዳብን አሰበና ያጋጠመዉን ችግር በሙሉ አንድም ሳያስቀር ነገረዉ። ነገር ግን ጓደኛዉ ኢዮናዳብ ክፉና ጠማማ ሰዉ ስለነበረ የማይገባ ክፉ ምክሩን ለአምኖን መከረዉ። እንዲህ ሲል፡- ምን ችግር አለዉ ታዲያ አሞኛል ብለህ ለአባትህ ለዳዊት ላክበት ሊያይህ ሲመጣ እህቴ ትዕማር ምግብ ታብስልልኝ ብለህ ንገረዉ አባትህ ዳዊትም ምንም ስለማይጠረጥር እርሷን በፍጥነት ይክልህል። ትእማር ምግቡን አዘጋጅታ ክፍልህ ይዛ ስትገባ የልብህን ታደርሳለህ ሲል ሰይጣናዊ ምክሩን ሹክ አለዉ። በዚህ ጊዜ አምኖን የጠማማ ጓደኛዉን ምክር ሰምቶ ለአባቱ ለዳዊት፤ አባዬ አሞኝ ተኝቻለሁ እህቴ ትዕማርም ትምጣና ታስታመኝ ምግቤን እያሰናዳች ታቅርብልኝ ትንከባከበኝ ሲል መልዕክት ላከበት። አባቱ ቅዱስ ዳዊትም የምር የታመመ ስለመሰለዉ ትዕማር እህቱን ላከለት። ትዕማር እህቱ እዉነት ወንድሟ የታመመ መስሏት መጥታ ምግቡን እንደሚወደዉ

አድርጋ አብስላና አዘጋጅታ አቀረበችለት ወደ ዉስጥ አስገቢዉ አላት ሀገር ሰላም ነዉ ብላ ያዘጋጀችለትን ምግብ ይዛ ወደ መኝታ ክፍሉ ስተገባ በቤት ዉስጥ ያሉትን አገልጋዮች በሙሉ አስዎጥቶ ሰይጣናዊ ምኞቱን ፈጸመባት፤ ከክብርም አሳነሳት እንዲያዉም ከክብር ካሳነሳት በኋላ መጀመሪያ ከወደዳት ይልቅ በኋላ የበለጠ ጠላት። ምክንያቱም ሀጢያት ከሰሩት በኋላ ያስጠላልና። ወዲያዉኑ አሁኑኑ ከክፍሌ ዉጭልኝ አላት። ተዉ ወንድሜ ከበፊቱ ይልቅ ያሁኑ የበለጠ ይጎዳኛል አለችዉ። ይሁን እንጅ ልመናዋን ከምንም ሳይቆጥር ከእልፍኙ ጎትቶ አዉጥቶ ወደ ዉጭ ጣላት። በዚህም የተነሳ በገዛ እህቱ ላይ ከበደል ሁሉ በላይ የከፋ በደልን ፈጸመባት። ዛሬም በዚህ በምንኖርበት አለም የብዙ እህቶቻችንና ወንድሞቻችን ህይዎት ሰይጣናዊ ምክርን በሚመክሩ እኩይ ጓደኞች አማካኝነት ሲበላሽ በአይናችን እናያለን በጆሮአችን እንሰማለን። ኢዮናዳብ ቅንና በጎ ህሊና ቢኖረዉ ኖሮ ስንኳን በእግዚአብሔርም በሰዉም ዘንድ አስቀያሚ የሆነዉንና ሲሰሙት እንኳን ለጆሮ የሚቀፍን ድርጊት በገዛ እህቱ ላይ እንዲፈጽምባት ለአምኖን ባልመከረዉም ነበር። ግን ምን ያደርጋል ከእባብ እንቁላል እርግብ እንደማይፈለፈል ሁሉ ከጠማማ ልብም መልካም ነገር አይመነጭምና እርሱ ተሳስቶ ጓደኛዉንም አሳሳተዉ፤ ከፍ ሲልም ምንም የማታዉቀዉን የትዕማርን ህይዎት አጨለመዉ። ዉድ ክርስቲያኖች የተዋህዶ ልጆች ለእኛ  የሚያስፈልጉን ጓደኞቻችነ ግን ጽድቅን ከምናገኝባት ከእግዚአብሔር ቤት ጎትተዉ የሚያስወጡን ሳይሆን ሀጢያትና ክፉ ስራ ከሚሰራበት ከአለማዊ ቦታ እጃችንን ይዘዉ እየጎተቱ ወደ ጽድቅ ቦታ የሚያስገቡን መሆን አለባቸዉ። ከጽድቅ ቦታ የሚያአስቀሩ ጠማማ ልብ ያላቸዉ ሰዎች አሉና። የልብ ጓደኛ ስንመርጥም ከዚህ አንጻር ተመልክተን በሰከነ አዕምሮ ልናስብበት ይገባል። «ከወደቁ በኋላ መፈራገጥ ለመላላጥ» እንደሚባለዉ በሀጢያት ከወደቅን በኋላ በሰራነዉ ስራ ደሞዛችንን የምንቀበለዉ እኛዉ ራሳችን እንጅ ያሳሳተን ሰዉ አደለምና ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል።

## 4ኛ/ የሮብአምና ጓደኞቹ ምክር (1ኛ ነገስት 12፡1 እስከፍፃሜ)

ንጉስ ሰሎሞን በአባቱ በቅዱስ ዳዊት እግር ተተክቶ እንደነገሰ ሁሉ ሮብአምም በአባቱ በሰሎሞን እግር ተተክቶ በእስራኤላዊያን ላይ ነገሰ። መቼም ቢሆን አንድ ሰዉ ከፍ ወዳለ ማዕረግ ሲደርስ በመጀመሪያ ለዚያ ክብር ያበቃዉን እግዚአብሔርን ቢያመሰግንና በቀጣይ ደግሞ በተመደበበት ቦታ ላይ የአገዛዝና የአሰራር ብልሀቱንና ጥበቡን እንዲሰጠዉ እግዚአብሔርን ቢጠይቅ የጥበብ ባለቤት የሆነዉ እግዚአብሔር ሁሉን ያስችለዋል። ከዚህም አንጻር የጎደለዉንና የሚያስፈልገዉን ሁሉን ቻይ የሆነዉን እግዚአብሔርን በመጠየቅ የተሳካለት ንጉስ ሰሎሞን ተጠቃሽ ነዉ። 1ኛ ነገስት 3፡6-9። ሮብአም በአባቱ በሰሎሞን ዙፋን ላይ እንደነገሰ እስራኤላዉያን ተሰብስበዉ በመሄድ በአባትህ ዘመን ቀንበር ከብዶብን፤ መከራዉ ጸንቶብን ነበር። አሁንም ንጉስ ሆይ ሽህ አመት ንገስ በአንተ የንግስና ዘመን

ቀንበሩን እንድታስወግድልን፤ መከራዉንም እንድታቀልልን እንለምንሀለን ብለዉ በጨዋ ወግ አደግድገዉ እጅ እየነሱ ልመናቸዉን አቀረቡለት። ሮብአምም በወቅቱ ሀሳባቸዉን ሰምቶ የሶስት ቀን ጊዜ ሰጡኝ መልሱን እነግራችኋለሁ በማለት አሰናበታቸዉ። ከዚያም በመጀመሪያ የሀገሩን ሽማግሌዎች ሰበሰበና ምን ላድርግ አላቸዉ። ሽማግሌዎችም ለዚህ ህዝብ እሽ በጄ ብለህ ብትገዛለት መልሶ ለአንተ ይገዛልሀል በዘመንህም ሁሉ ባሪያም ይሆንልሀል አሉት። ቀጠለና ጓደኞቹን ጠርቶ አባትህ ቀንበር አክብዶብናል ለሚለዉ ለዚህ ህዝብ ምን እንድመልስለት ትመክሩኛላችሁ? አላቸዉ። ጓደኞቹ የመከሩት ምክር ግን የሚገርም ነበር። ሁ በላቸዉ፤ ለዚህ ህዝብ ፊት አትስጠዉ እንደ ሰም አቅልጠህ አንደ ሸክላ ቀጥቅጠህ ግዛዉ በማለታናሽቱ ጣቴ ከአባቴ ወገብ ትወፍራለች። አሁንም አባቴ ቀንበር ጭኖባችኋል፤ እኔ ግን በቀንበራችሁ ላይ እጨምራለሁ፤ አባቴ በአለንጋ ገርፏችኋል፤ እኔ ግን በጊንጥ እገርፋችኋለት ክፉ ምክራቸዉን መከሩት። በመጨረሻም በቀጠሮዉ መሰረት ህዝቡ ሁሉ የሮብአምን መልስ ሊሰማ መጣ። ሮብአም ግን ሽማግሌዎች የመከሩትን ጥሩ ጥሩ ምክር ትቶ ወጣት ጓደኞቹ የመከሩትን ምክር ነገራቸዉ እንዲህ ሲል፡- አባቴ ቀንበር ጭኖባችኋል፤ እኔ ግን በቀንበራችሁ ላይ እጨምራለሁ፤ አባቴ በአለንጋ ገርፏችኋል፤ እኔ ግን በጊንጥ እገርፋችኋለት በማለት። በዚህ ጊዜ የእስራኤል ህዝብ ሆ ብሎ አመጸበት ከዙፋኑም አሰደዱት በገዛ እጁም ዉርደትን አንደ ጋቢ ተከናነባት። ለምን ቢሉ በክፉ ጓደኞቹ ምክር ስለተመራ ነበር። ዛሬም ቢሆን ብዙዎች ከምንም ተነስተዉ ወደ ስልጣን ሲመጡ የማይገባ ስራ እንዲሰሩና ያልሆነ ዉሳኔ እንዲዎስኑ ክፉ ምክር የሚመክሯቸዉ ጠማማ አመለካከት ያላቸዉ የገዛ ጓደኞቻቸዉ ናቸዉ። የኋላ የኋላ ግን ከስልጣን መባረርና ከስራ መፈናቀል ሲመጣ በዙሪያዉ ቆመዉ አፍን ከመክፈትና ጣትን ከመቀሰር ዉጭ አንዳች ነገር ሲፈይዱላቸዉ አይታዩም። ለምን ቢሉ ከአለማዊና ጠማማ ልብ ካለዉ ጓደኛ መልካም ነገር አይጠበቅምና። ስለሆነም እኛም ጓደኛ ብለን የምንይዛቸዉ ሰዎች ቅን ምክር የሚመክሩን እንጅ ጠማማና ክፉ ምክርን እየመከሩ ከእግዚአብሔር ልጅነት፤ ከቅድስት ቤተክርስቲያን አገልግሎትና ዘላለማዊ ድነትን ከምናገኝበት ከቅዱስ ስጋዉና ከክቡር ደሙ የሚለዩን ሰዎች እንዳይሆኑ እጅግ ልንጠነቀቅ ይገባል።

## 5ኛ/ የእስራኤላዉያንና የሙአብ ልጆች ጓደኝነት (ዘፍ 25፡1)

እግዚአብሔር አምላክ በብዙ ተአምራት፤ የኤረትራ ባህርን ከፍሎ እስራኤላዉያንን ከግብፅ ባርነት እንዳወጣቸዉ ሁላችንም እናዉቃለን። እስራኤላዉያን ግን ብዙም ሳይቆዩ የኤርትራ ባህርን ተሻግረዉ ወደ ተስፋዋ ምድር ጉዞ በሚያደርጉበት ወቅት ሞአብ የምትባል ሀገር እንደደረሱ የሞአብ ንጉስ ባላቅ በሰማ ጊዜ በልአም የተባለን ሀብተ መርገም የተሰጠዉን ሰዉ ጠርቶ እስራኤላዉያን ሀገሬን እንዳይዙ በእኔም ላይ ጥቃትን እድአይፈጽሙብኝ እርገምልኝ

አለዉ። በልአም አስቀድሞ በእግዚአብሔር መልአክ እንደተነገረዉ ይህ ህዝብ የእግዚአብሔር ህዝብ ነዉና ልረግመዉ አልችልም ይልቁስ አምላካቸዉ አግዚአብሔር በአምልኮቱ ቀናተኛ ስለሆነ አንድ መላ ልንገርህ ሲል ክፉ ምክሩን ለባላቅ ሹክ አለዉ። ባላቅም ከበልዓም በተመከረዉ ምክር መሰረት ቆንጆ ቆንጆ ሴቶች ልጃገረዶችን ወደ እስራኤል ሰፈር ላካቸዉ። የእስራኤልም ወንዶች ባዩአቸዉ ጊዜ ደስ አላቸዉ። መጀመሪያ መዳራትና መተሻሸት ጀመሩ መዳራት የዝሙት ዋዜማ ነዉና በመቀጠልም ከእነሱ ጋር በዝሙት ረከሱ። ለምን ቢሉ መዳራት ያረክሳልና። ጌታችንና አምላካችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዉን ከእግዚአብሔር መንግስት ከሚለዩት ነገሮች አንዱ መዳራት ነዉ እንዳለን በቅዱስ ወንጌሉ። በመጨረሻም ይህም አልበቃ ብሏቸዉ ለጣኦት የሰዉትን መስዋዕት እነዲበሉ አደረጓቸዉ። ብርሃናተ አለም ቅዱስ ጳዉሎስ በ2ኛ ቆሮ 6፥14 ላይ ከማያምኑ ጋር በማያመች አካሄድ አትጠመዱ፤ ጽድቅ ከአመጻ ጋር ምን ተካፋይነት አለዉና? እንዳለን ህዝበ እግዚአብሔር የተባሉት የእስራኤል ልጆች ለጣዖት የተሰዋን እርኩስ መስዋዕት ስለበሉና በእምነት ከማይመስሏቸዉ ከአህዛብ ልጆች ጋር በዝሙት ስለወደቁ በአንድ ቀን ብቻ ሃያ አምስት ሽህ የሚሆኑት ሰዎች በእግዚአብሔር ቁጣ መቅሰፍት እንደ ቅጠል ረገፉ። ልብ እንበል በእስራኤላዉያን ላይ ይህንን መቅሰፍት የመጣባቸዉ ከአህዛብ ሴቶች ልጆች ጋር የመሰረቱት ጓደኝነት ነበር። እኛም በክርስቶስ ክርቲያን በወልድ ዉሉድ የተሰኘን ኦርቶዶክሳዉያን ሀይማኖት ከሌላቸዉ፤ ከአረማዉያንና ከመናፍቃን ጋር ጓደኝነት መመስረት አያስፈልገንም። ምናልባትም በስራ ጉዳይ ልንገናኝ እንችላለን። ነገር ግን ስራችንን ሰርተን ዘወር ማለት አንጅ አብሮ ምሳ መብላት፤ አብሮ ሻይ መጠጣት፤ አብሮ ወጣ ገባ ማለትና አላስፈላጊ ግንኙነቶችን መፍጠር ወደድንም ጠላንም ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ሳናዉቀዉ ወደዚያ ወደ ክፉ ስራቸዉ ልንሳብ፤ ሲዉል ሲያድርም ኑፋቄያቸዉ መርዞን ከክርስትና ህይዎታችን ልንለይ እንችላለን።

## 6ኛ/ የንጉስ ሰሎሞንና የፈርዖን ልጅ ጓደኝነት (1ኛ ነገስት 11፥1)

ንጉስ ሰሎሞን እግዚአብሔር አምላክ እንደ ልቤ የሚሆን የእሴይን ልጅ አገኘሁ ብሎ የመሰከረለትና የሰባት ሀብታት ባለቤት የሆነዉ የልበ አምላክ የቅዱስ ዳዊት ልጅ ነዉ። ይሁን አንጅ ንጉስ ዳዊት ለአርባ አመታት በእስራኤላዉያን ላይ ነግሶ በኖረበት ዘመን አካሄዱን ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር በማድረጉ በጸጋ ላይ ጸጋን በበረከት ላይ በረከትን ተጎናጽፎ በክብር ላይ ክብርን በሀብት ላይ ሀብትን ደራርቦ ከኖረበት የንግስና ዘመኑ እድሜን ጠግቦ እንደ አባቶቹ ሲያንቀላፋ በእርሱ እግር ልጁ ሰሎሞን የአባቱን መንበር ተተክቶ እስራኤላዉያንን ማስተዳደር ጀመረ። በመጀመሪያም ይህን ህዝብ በምን አቅሜ አስተዳድረዋለሁ ሲል አስቀድሞ ከእግዚአብሔር ጥበብን ለመነ። 1ኛ ነገስት 3፡7-9። በዚህም እግዚአብሔር አምላክን ደስ አሰኘ። እግዚአብሔርም አለዉ ፍርድን ትለይ ዘንድ ለመንክ እንጅ

ባለጸግነትንነና የጠላቶችህን ነፍስ ሳትለምን ይህን ነገር ለምነህልና እንደ ቃልህ አድርጌልህ አለሁ እነሆ ማንም የሚመስልህ ከአንተ በፊት እንደሌለ ከአንተ በኋላ እንዳይነሳ አድርጌ ጥበበኛ አስተዋይ ልቦና ሰጥቼሀለሁ። ፩ኛ ነገስት 3፡10-13። የተባለና ለእግዚአብሔር ቤተመቅደስ የሰራና እግዚአብሔር አምላክ ሁለት ጊዜ ተገልጦ ያነጋገረዉ ንጉስ ነበር። ይሁን አንጅ ጊዜ አልፎ ጊዜ ሲተካ ጓደኛ መምረጥ ላይ ትልቅ ስህተትን ፈጸመ። ከአህዛብ ወገን ከፈርዖን ሴት ልጅ ጋር ጓደኝነትን መሰረተ። እሷም ቤተሰቧም አረማዊና ጣዖት አምላኪዎች፤ ለጣዖት የሚሰግዱና ለጣዖት የሚንበረከኩ፤ ለጣዖትም መስዋዕት የሚያቀርቡ ነበሩ። የፈርዖን ልጅ ግን ቀስ በቀስ ልቡን በፍቅር አሳብዳ እንዲጠብቀዉና እንዲያከብረዉ ከደጋግ ቅዱሳን ወገኖቹ ጀምሮ እስከ አባቱ እስከ ቅዱስ ዳዊት ድረስ የሚመሩበትን የእግዚአብሔርን ህግ አንዲረሳና ለራሷ ጣዖት አንዲንበረከክ፤ የጣዖትንም መስዋዕት እንዲበላ፤ አልፎ ተርፎም ለምታመልከዉ ጣዖት ቤተ ጣዖትና መሰዊያ እዲሰራ አደረገችዉ። ሰለሞንም የእግዚአብሔርን ቤተመቅደስ ሰርቶ የተመሰገነበትን እጁን ቤተ ጣዖት ሰርቶ አረከሰዉ። በዚህም የተነሳ የእግዚአብሔርን ፍቅር በጣዖት ፍቅር ለወጠዉ፤ ነፍሱንም ስጋዉንም ህሊናዉንም ለአምልኮተ ጣዖት በማስገዛት እግዚአብሔር አምላክን አሳዘነዉ። ኀልማሳ በሚስቱ፤ እግዚአብሔር በአምልኮቱ ሲገቡበት አይታገስምና እንዲህ አለዉ፤ መንግስትህንና ስልጣንህን ቀድጄ ለባሪያህ እሰጣለሁ። ዛሬም አንዳንዶች ከእናት ቤተክርስቲያናቸዉ ከኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሀይማኖታቸዉ ዉጭ በማየት በእምነት ከማይመስሏቸዉ ሰዎች ጋር ገጥመዉ ከወደድሽኝ እኛ ቸርች ነይ፤ ከወደድከኝ እኛ ቸርች ና እያሉ ከያዙት እዉነተኛ የህይዎት መንገድ ከቅድስት ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እያስወጡ ወደ እስልምናና ወደ ተለያዩ የመናፍቃን የእምነት ድርጅቶች የሚወስዱ፤ እየሄዱም በነፍስም በስጋም የሚጠፉ ብዙዎች ናቸዉ። ይህም ማለት ከጠማማ ጋር ዉሎ ጠማማ ሆኖ መገኘት ማለት ነዉ።

## 7ኛ/ የሶምሶምና የደሊላ ጓደኝነት (መጽሐ. መሳፍንት 16፡15)

ማኑሄና ሚስቱ ልጅ ያልነበራቸዉ መካኖች ነበሩ። ይሁን እንጅ እግዚአብሔር አምላክ በረድኤቱ ሲጎበኛቸዉ መልአኩን ልኮ ለማኑሄ ሚስት ተገለጠና ወንድ ልጅ እንደምትወልድ፤ ከህጻንነቱ ጀምሮ ለእግዚአብሔር እንደሚለይ፤ የሚያሰክር ነገርም እነደማይጠጣ፤ በራሱ ላይም ምላጭ እንደማይዞርና ናዝራዊ ተብሎ እንደሚጠራ፤ እስራኤላዉያንን ከፍልስጤማዉያን እጅ ማዳን እንደሚጀምር ነገራት። በኋላም የጠየቁትን የማይነሳ፤ የተናገረዉን የማይረሳ አምላክ በጊዜዉ ወንድ ልጅን ሰጣቸዉና እናቱ ሶምሶን ብላ ስም አወጣችለት። ሶምሶንም ሀይለ እግዚአብሔር የተሰጠዉ ሰዉ ስለነበረ ምንም አይነት ስለት በእጁ ሳይዝ የአንበሳ ደቦል ቡጭቅጭቅ አድርጎ የገደለ ከዚህ በላይ በአህያ መንጋጋ ብቻ አንድ ሽህ ሰዉ እንደፈጀ ታሪኩ ይነግረናል። መጽ. መሳፍንት 15፡15-16። በመጨረሻ ግን ይህ

ለእግዚአብሔር የተለየ ሀያል ሰዉ ለእግዚአብሔር የተለየበትን ሰዉነቱን ይዞ ሴተኛ አዳሪ ጋለሞታ ቤት ገባና ደሊላ ከተባለች ሴት ጋር ጓደኝነት በመመስረት አብሮ መዋል፤ አብሮ ማደር ጀመረ። ፍልስጤማዊቷ ደሊላም ቀስ በቀስ በፍቅሯ እያንበረከከች፤ ልቡን ወደ እርሷ እየሳበች፤ የልቡን እንዲያደርስ ከፈቀደችለት በኋላ የግል ታሪኩንና ሀይል ስላገኘበት ምስጢር ምንነት ማዉጣጣት ጀመረች። ሶምሶን ግን ምስጢሩን ለደሊላ ሳይናገር ለጥቂት ቀናት ብቻ ቆየ። የኋላ የኋላ ግን የሀይሉ ምስጢር ጸጉሩ ላይ እንዳለና ሲወለድ ጀምሮ ራሱ ላይ ምንም አይነት ምላጭ እንዳላረፈበትና ጸጉሩን ቢላጭ ግን ሀይሉን እንደሚያጣ ምስጢሩን አንድም ሳያስቀር ዘርግፎ ነገራት። ደሊላም ፍልስጤማዉያንን በቤቷ ጓዳ ደብቃ ድብን ብሎ እንቅልፍ በተኛበት ጸጉሩን ሙልጭ አድርጋ ላጨችዉ። በማስቀጠልም ፍልስጤማዉያን መጡልህ አለችና ቀሰቀሰችዉ። ሶምሶን ግን  እሱ፤ ወላጆቹና የመወለዱን ምስራች የተናገረዉ የእግዚአብሔር መልአክ ብቻ  የሚያዉቁጥን ምስጢር አሳልፎ ለአህዛብ ሰጥቷልና እንደ ቀድሞዉ ፎክሬ እነሳለሁ ሲል ሀይሉ ደካማ፤ ጉልበቱ ቄጠማ ስለሆነበት ሳይቻለዉ ቀረ። ፍልስጤማዉያን ይዘዉ አይኖቹን አወጡ። ድመት አይጥን የዛ ስትጠግብ እንደ ኳስ እየወረወረች እንደምትጫወትበት መጫወቻ አድርገዉ ገደሉት። እኛስ ከዚህ ምን እንማራለን? ብዙ ጊዜ ጓደኛ ብለን በያዝናቸዉ በእምነት በማይመስሉን ሰዎች ሀይማኖትን የሚያስክዱ ፈተናዎች ቢቀርቡልን የምንታገሰዉ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ሊሆን ይችላል። ሲዉል ሲያድር ግን ማንም ይሁን ማን ሌላዉ ቢቀር በመንፈሳዊ ህይዎት የጠለቀ እዉቀት አለኝ የሚል ሰዉም ቢሆን እንኳን መልካም ጓደኛ እስካልመረጠ ድረስ መዉደቁ አይቀርም። የሶምሶንም ህይዎት የሚያስተምረን ይህንኑ ነዉ። ስለሆነም በዚህ እስካሁን እያየነዉ በመጣነዉ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ዉስጥ የጓደኛ አያያዝ መመዘኛችን ምን ሞሆን እንዳለበት ከቃለ እግዚአብሔር በተረዳነዉ መሰረት ሊሆን ይገባል። መቼም ቢሆን የሰዉ ልጅ የልብ የሚለዉ ጓደኛ ሊኖረዉ ይገባል። ከዚህ አንጻር የምንይዛቸዉ ጓደኞቻችን ካለብን መንፈሳዊ ዝለት አላቅቀዉ ከፍ ወዳለ መንፈሳዊ ጥንካሬን ሊጨምሩልን ይገባል እንጅ ጥቂትም ቢሆን ከነበረን መንፈሳዊ ህይዎት የሚያራቁቱን፤ እንደ ሶምሶን ከልጅነታችን ጀምሮ ይዘነዉ ያደግነዉን አዕማደ ምስጢራትን ከልባችንና ከነፍሳችን እንድናወጣ የሚያደርጉ ቢፀ-ሀሳዊያንን ጓደኛ ማድረግ አይገባንም። ስለሆነም በመልካም ጓደኛ ተመክረን መልካም ስራን ሰርተን፤ ከክፉና ጠማማ ጓደኛ ተጠብቀንና በተዋህዶ እምነታችን ጸንተን የመንግስቱ ወራሾች ለመሆን እግዚአብሔር ይርዳን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ደንግል ወለመስቀሉ ክቡር አሜን!

ተዘጋጀ፡-

በሄልሲንኪ አቡነ ተክለሃይማኖት ቤተክርስቲያን ስብከተ ወንጌል ክፍል ጥር ወር 2010 ዓ.ም